## ሐምሌ 5 2008 ዓ.ም በአማራ ሕዝብ ላይ የተቃጣ ጥቃት የተመከተበት ቀን!!




## ሐምሌ 5!!!

### (የሺህሳብ አበራ)

ከወር በፊት ፌዴሬሽን ምክር ቤት በር ላይ አዲስ አበባ ተይዘው ከአስመራ ያዝናቸው ተብለው ታሰሩ፡፡ወደ ማዕከላዊ ገቡ፡፡

እንዳይደገማችሁ ተብለው በአንድ ቀን ተለቀቁ፡

እንዳይደገማችሁ የተባለውን የማንነት ጥያቄ ህገመንግስቱን ተከትለው ቀጠሉ፡፡

ኮሚቴውን በአሸባሪነት ፈርጆ ወደ እስር ማስገባት መፍትሄ ሆኖ ተበጀ፡፡

መጀመሪያ የኮሚቴውን ሰብሳቢ ኮሌኔል ደመቀ ዘውዱን ሃምሌ አራት ለመያዝ ታቀደ፡፡

በዕቅዱ መሰረት ሃምሌ አራት ንጋት 10:00 ኮሌኔል ህሉፍ በሚባል ኮሌኔል የሚመራ ጦር ተላከ፡፡

"ኮሌኔል ደመቀ ከቤት ውጣ ተባለ" ባለቤቱ አይወጣም ብላ ፍርጥም ብላ መለሰች፡፡

ቤቱን በሌሊቱ መውገር ጀመሩ፡፡

ኮሌኔል ደመቀ ወደ ዞኑ አስተዳደር እና ፀጥታ ደውሎ " ቤቴ በወታደር ተከቧል፡፡ እናንተ ናችሁ የላካችሁብኝ?" ሲል ተረጋግቶ ይጠይቃል፡፡

የዞኑ አስተዳደር እና ፀጥታ ሃላፊ "ከአማራ ክልል የፀጥታ ዘርፍ ማንም አንተን ለመያዝ ያሰበም፣ የተላከም የለም" ሲል እንቅጩን ይናገራል፡፡

ንጋት 11:00 ጀምረው በኮሌኔል ደመቀ እና በቤተሰቡ ላይ ተኩስ ከፈቱ፡፡

ሻወር ቤት ሆኖ ለተኩሱ ምላሽ ሰጠ፡፡

በምላሹ ዓምስቱ ወዲያው ተገደሉ፡፡

ዓምስቱ ጓደኞቹ የተገደሉበት የቡድኑ መሪ፣ ኮሌኔል ህሉፍ በንዴት ዘሎ ወደ ጣራው አካባቢ ወጥቶ ወደ ታች አልሞ ይተኩስ ጀመር፡፡

ወዲያው ያለመበት ዓይኑን ተመቶ ወደቀ፡፡ ኮሌኔል ህሉፍ አንዳርጋቸው ፅጌን ከየመን አፍኖ ያመጣው ግዳጅ ፈጣሚ ነበር፡፡ ግዙፍ እና ህቡዕ አፈናዎች በኮሌኔል ህሉፍ በኩል ያልፉ ነበር፡፡ "የአፈናው ቡድን ቅስም ሃምሌ 5 ቀን ተሰበረ፡፡"

ተኩሱ እስከ ሃምሌ ዓምስት ጠዋት ቀጥሎ የበለሳ ሽፍታ አልያዝ ብሏል ተብሎ ህዝቡ ኮሌኔልን ለመያዝ ተረባረበ፡፡ ወዲያው ግን እውነቱ ተገለጠ፡፡የበለሳ ሽፍታ ሳይሆን የወልቃይት የማንነት ጠያቂው ኮሌኔል ደመቀ እንደሆነ ተሰማ፡፡ ከወልቃይት እስከ አርማጮ ህዝቡ ወደ ጎንደር ከተማ ገብቶ ከበባ ጀመረ፡፡

ሃይል እንዲጨመራቸው አፋኝ ቡድኑ ጠየቀ፡፡ የወቅቱ ኤታማጆር ሹም ኮሌኔል ደመቀ ያለበት ቤት በቦንብ እንዲመታ ትዕዛዝ ሲያስተላልፉ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ደመቀ መኮንን " አይቻልም፡፡ ሙሉ ሃላፊነቱን አንተ ትወስዳለህ፡፡ እምቢ ብለህ ካደረግኸው ውርድ ከራሴ" ብለው ሳሞራን ሞገቱ፡፡

አቶ ገዱ አንዳርጋቸው ኮሌኔል ደመቀ ከተነካ" የአማራ ህዝብ ጉዳዮን ተናግሬ ከስልጣን እለቃለሁ" ሲሉ አስጠነቀቁ፡፡

በዚህ ምክንያትም የኮሌኔል ጉዳይ በህዝቡ ዳኝነት እንዲያዝ ተወስኖ በጓደኞቹ አማካኝነት ተያዘ፡፡

በከተማው ወጥቶም ተንቀሳቀሰ፡፡

በህዝቡ እና በጓደኞቹ ፈቃድ ወደ እስር ገባ፡፡

የኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ የኮሌኔሉ ጉዳይ በጎንደር ባለው ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲታይ ቢወስንም፣ወደ ማዕከላዊ ለመውሰድ ሙከራ ተደረገ፡፡ ከሸፈ፡፡

በ 46 ሰው ነፍስ ግድያ ተከሰሰ፡፡ የነፍስ ግድያው በሽብር ተያዘ፡፡ በአሸባሪነት ተከሰሰ፡፡ ብዙ ክሶች ውድቅ ሲደረጉ፣ ዳኛው ችሎት ላይ ተይዞ ታሰረ፡፡

ዳኛው ወዲያው ተለቀቀ፡፡ኮሌኔሉም እንደዛ፡፡

ሃምሌ ዓምስት በዚህ ምክንያት የአማራ ብሄርተኝነት እና የአማራነት ፅንሰ ሃሳብ ማሟሟቂያ ሆነች፡፡ ዘጋርዲያን የስራዓቱ አከርካሪ ተመታ፡፡ በጎንደር በኩል ቅዋሜ ከተነሳ ስራዓቱ አይቀጥልም ሲል፣ ቢቢሲ ደግሞ በአማራ ክልል ዋና ከተማ " ጎንደር" በመንግስት ላይ የተነሳው አብዮት ስራዓቱን እየበላው ነው ሲል ዘገበ፡፡ (ቢቢሲ ጎንደርን ዋና ከተማ ብሎ የዘገበው በስህተት ነው፡፡ የአማራነት ጉዳይ ቀድም በጎንደር ስለተንሸራሸረም ይሆናል፡፡)

ከሃምሌ ዓምስቱ በኃላ ህዝባዊ ማዕበሉ፣ ሃምሌ 24 በጎንደር፣ ነሀሴ 1 በባህርዳር እያለ መላው የአማራ ክልልን አዳረሰ፡፡



ሐምሌ **5 2008** ዓ.ም በአማራ ሕዝብ ላይ የተቃጣ ጥቃት የተመከተበት ቀን በጎንደር ከተማ እንዲህ ታስቦ ውሏል**!! July 12 2018**



ሐምሌ **5 2008** ዓ.ም በአማራ ሕዝብ ላይ የተቃጣ ጥቃት የተመከተበት ቀን በጎንደር ከተማ እንዲህ ታስቦ ውሏል**!! July 12 2018**



ሐምሌ **5 2008** ዓ.ም በአማራ ሕዝብ ላይ የተቃጣ ጥቃት የተመከተበት ቀን በጎንደር ከተማ እንዲህ ታስቦ ውሏል**!! July 12 2018**